# የሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ሜሪላንድ የኮቪድ የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ሰነድ ማረጋገጫ ዝርዝር

በሚያመለክቱበት ጊዜ የሚከተሉትን ሰነዶች ለመጫን (ለማስገባት) ዝግጁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

## ☐ የፎቶ መለያ፤ መታወቂያ

- **የመንጃ ፍቃድ ኮፒ ወይም**
- **የስቴት መታወቂያ ኮፒ ወይም የፓስፖርት ኮፒ ወይም**
- **ሌላ ለእያንዳንዱ አዋቂ የቤተሰብ አባል ይፋዊ የፎቶ መታወቂያ**

## ☐ የአድራሻ/የነዋሪነት ማረጋገጫ

ቢያንስ ከኦገስት 2021 ጀምሮ በካውንቲው ውስጥ ለእርዳታ በሚያመለክቱበት አድራሻ ስለመኖርዎ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። ይህንን በባንክ ስቴትመንት፣ በኦፊሴላዊ የፖስታ መልእክት፣ በፍጆታ ክፍያ ወይም ሌላአድራሻዎን በሚያረጋግጥ ሰነድ ማድረግ ይችላሉ።.

## ☐ የገቢ ማረጋገጫ

- **የተከራይ ገቢ እና የብቁነት ማረጋገጫ (ይህም በድህረ ገጹ ላይ እና በማመልከቻው ውስጥ ይገኛል)**

በፕሮግራሙ የቤተሰብ የገቢ ገደብ ውስጥ መሆንዎን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማረጋገጫ ወይም በእርስዎ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። የ2020 ወይም 2021 የግብር ተመላሽ ወይም ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ ያሉ ሰነዶችን ያቅርቡ። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤

- **የክፍያ ማስረጃ (ፔይ ቼክ)**
- **የባንክ ስቴትመንት**
- **የሥራ አጥነት ክፍያ መግለጫዎች (ስቴትመንት)**
- **የአይአርኤስ (IRS )1040 ቅጽ ለ2020 ወይም 2021 አመት ፋይል የተደረገበት**
- **ከጃንዋሪ 1 ፤ 2020 ጀምሮ ወይምበኋላ ገቢ ላይ ተመርኩዞ የተወሰነ የፌዴራል ወይም የስቴት ፕሮግራም ደብዳቤ፣ ወይም ከኮቪድ በፊት እና አሁን ያለውን ገቢ በግልፅ የሚያመለክት የጽሁፍ መግለጫ**

## ☐ የኪራይ መረጃ

**የኪራይ ሃላፊነትዎን ፣የክፍያ ታሪክዎን እና ያለብዎትን የኪራይ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ይህም በኪራይ ደብተር፣ በሊዝ ወይም ከሌሎች ሰነዶች ጋርበመሆን አስፈላጊውን መረጃ የሚሰጥ ነው።**

**አሁኑኑ ያመልክቱ ፤ www.mc311.com/rentrelief**